# ስለ ቀጣዩ ትግል ማስታወሻ

## (ለህብረቱ አመራር ከመኢሶን የቀረበ)

አሁን ከፊታችን "አጣዳፊ" መስሎ የተደቀነው ጥያቄ ፓርላማ መግባት ወይስ አለመግባት የሚለው ጥያቄ ነው። በኛ በኩል ይህ ቁምነገር ያለውና ብዙዎችን አስጨንቆ የያዘ ችግር ቢመስልም በተለይ ከቀጣዩ ትግል አንፃር ሲታይ ዋናውና አንገብጋቢው ጥያቄ ሆኖ ሊቀርብ የሚችል አይመስለንም። ህዝባችን ሞቶ ተሰውቶ፤ መርጦና አሸንፎ በመስዋእትነት ያገኘሁትን ድል በሸፍጥ ተነጠቅሁ ይላል። ይህ ድሉም እንዲረጋገጥለት ይፈልጋል። ይህንንም ለማረጋገጥ የሚያስፈልገውን ሁሉ ትግል ለማድረግ ዝግጁነቱን በም-ንም አይነት በማያሻማ ሁኔታ አረጋግጧል። አለም አቀፍ ኮሙኒቲውም አንደኛ የግንቦቱ ምርጫ ከኢትዮጵያ ህዝብ የዴሞክራሲ ጥማት የሚመጥንም አልነበረም ሁለተኛ ደግሞ በአለም አቀፍ ደረጃም ስለነፃ ምርጫ የተደነገጉትን መስፈርቶች አያሟላም በማለት የህዝቡን "የተጭበረበርኩ" ስሜት አጠናክሮታል። ተቃዋሚ ሃይሎችም ቢሆኑ ምርጫው ተጭበርብሩዋል፤ የህዝቡ ድም-ፅ ይከበር እያሉ በያለበት እያስተጋቡ ናቸው።

ዋናው የወቅቱ ጥያቄ ይህንን የህዝብ ድል ለማስመለስ የሚደረገውን ሰላማዊና ህጋዊ ትግል እንዴት እንምራው የሚል ጥያቄ ነው። መነሻው ነጥብ ድል ከፈለግን ት-ግሉን እዚህ ታሪካው ደረጃ ያደረሰው ህዝባዊ እንቅስቃሴ በምንም አይነት መብረድ የለበትም የሚል መሆን ይኖርበታል። ከዚህ አልፈን ደግሞ ይህ ትግል መስፋት አለበት ብለን ከፖለቲካ ውጭ ያሉ የተደራጁም ያልተደራጁም ሃይሎች እንዲደባለቁት ያለማሰለስ መስራት ያስፈልጋል። መቋጠር አለበትም ብለን በሃገር አቀፍ ደረጃ በአንድ በሆነ አገር አቀፍ አስተባባሪ አካል መቀነባበር አለበት በሚለው መፈክር ስር መንቀሳቀስ ይኖርብናል። ባጭሩ የመጨረሻው ድላችን ዋስትና የህዝባች ያልተቋረጠና ከእለት እለት ይበልጥ እየተደራጀ የሚሄድ ትግል ነው እንላለን። ከዚህ ውጭ የድል ተስፋ የለም ብቻ ብለን አናቆምም። በዚህ የህዝብ ትግል የተደናገጡት የኢህአዴግ መሪዎች በምንም ይሁን በምን ምክንያት ይህንን ትግል ከፋፍለውና አዳክመው ካቀዘቀዙት ያለአንዳች ጥርጥር የከፋኛ ቅልበሳ አደጋ አለ። ያለማቋረጥ ወደፊት የሚቀጥልበት ሁኔታ ካልተፈጠረና ወደፊት ካልቀጠለ በየትም ጊዜ ይሁን በየትም በኛም ሆነ በሌሎች አገሮች ታሪክ እንደታየው መንቀሳቀስ ጀምሮ ጋብ የሚል ህዝባዊ እንቅስቃሴ ይቀለበሳል። ይህ ቅልበሳ ከመጣና በምንም ምክንያት ይሁን በምን ይህ የተንቀሳቀሰ ህብረተሰብ ትጥቁን ከፈታ ሃገራችንና ህዝባችን ዘግናኝ የሆነ በቂም በቀል የአፈና ውርጅብኝ ወቅ-ት ውስጥ ይገባሉ። ይህ አይነቱ የትግልን ሽንፈት የሚከተል የአፈና ውርጅብኝ ሩቅ ሳንሄድ ባለፈው 1992 ዓ..ም. ምርጫ ማግስት ህዝባችንን ያጋጠመው ክስተት ነው።

ፓርላማ መግባት ወይም አለመግባት የሚለውን ጥያቄ የምንመልሰው ከዚህ እውነታ ተነስተን ነው። በመሰረቱ የአንድ ህዝብ የነፃነት ተጋድሎ እንደ ሁኔታው በፓርላማም ውስጥ ከፓርላማም ውጭ ባለ ትግል ተጋግዞና ተቀነባብሮ መቀጠሉ የትም ያለ አሰራር ነው። ዛሬ ባለንበት የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ግን በቀረው አለም እንደሚታየው ሁለቱ ዘርፎች የሚተጋገዙበት ሳይሆን የሚጠፋፉበት አካሄድ ስለሆነ ከሁለቱ አንዱን መምረጥ የግድ ይላል። ፓርላሜንቱ ራሱ የህዝብ ድምፅ ተሰርቆ፤ ህገ መንግስት ተረግጦ የተቋቋመ የድምፅ ሌቦች ዋሻ ስለሆነ እዛ ውስጥ ተገብቶ ምንም የሚፈየድ ነገር ያለ አይመስለንም። ትልቁ አደጋ ግን ይህ "የፓርላሜንታዊ ተቃውሞ" ፋይዳ ቢስነት አይደለም። ፓርላሜንት መግባትን መቃወም የሚያስፈልግበት ምክንያት "እዛ ተገብቶ ለትግሉ ሳንቲም አስተዋፅኦ ማድረግ አይቻልም" የሚለው ምክንያት ብቻ ቢሆን ኖሮ እስከዚህም የሞት ሽረት ጥያቄ አድርገን አናየውም ነበር። "የፓርላሜንታዊ ተቃውሞ" ከዚህ ፋይዳቢስነት አልፎ ለህዝባችን ትግል መዘዝ አለው ብለን እንሰጋለን። ተቃዋሚ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎችን በመከፋፈል፤ የህዝቡን ትግል ግራ በማጋባት፤ ለዚህ ለኢህአዴግ ህ-ገ ወጥ አካል የህጋዊነት ፍንጭ በመስጠት፤ የኢህአዴግ መሪዎች የተቃዋሚውን ጎራ በአንድ በኩል መመታት ባለባቸው ህገ ወጥ አክራሪዎችና በሌላ በኩል ደግሞ ህግ አክብረው በሚንቀሳቀሱ የተከበሩ ተቃዋሚዎች ፈርጀው በህዝባችንና በታጋይ ልጆቹ ላይ በአመፅ እንዲሰማሩ በሩን በርግዶ የሚከፍት፤ እንዲህ አይነቱ አፈራረጅ በአለም አቀፍ ኮሙኒቲውም ተቀልቦ የዚህን መከረኛ ህዝብ ተጋድሎ ለአደገኛ ብቸኝነት የሚዳርግ አደገኛ አካሄድ ነው። ባጭሩ በኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ "ፓርላሜንታዊ ተቃውሞ" እና ከፓርላሜንት ውጭ ተቃውሞ የሚባሉት ሁለቱ የሚጠፋፉ

የትግል ዘርፎች መሃከል መምረጥ ያስፈልጋል። የሃገራችን ዴሞክራቶች ያለማወላወል በህዝባዊ ትግል ብቻ የሚተማመን ሰላማዊና ህጋዊ የትግል ጎዳና መያዝ ይኖርባቸዋል።

በድርድሩም ጉዳይ ቢሆን ህዝቡ ታግሎና አይሎ ከኢህአዴግ ሊፈልቅቅ የሚችላቸውን ድሎች (ኮንሴሽንስ) እሱን ተወውና እኛ ተደራድረን እናስገኝልሃለን የሚባል ከሆነ ይህም የሚያዋጣ አካሄድ አይመስለንም። ይህ ድርድርን መቃወም አይደለም። ከኢህአዴግ ጋር መደራደር ያስፈልጋል። የድርድር ሂደት ከፓርላማው መግባት አለመግባት ጥያቄ ይለያል። ከፍ ብለን እንዳልነው በሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሁለቱ የትግል ዘርፎች ተጋግዘው የሚራመዱበት መንገድ የለም። ድርድርና ህዝባዊ ትግል ግን በአንድ ላይ ሊካሄዱ ይችላሉ ብቻ ሳይሆን ሳይነጣጠሉ መካሄድ ይኖርባቸዋል እንላለን። ግን ደግሞ ይህ አካሄድ በአንድ በኩል በኛው በተቃዋሚዎች ጎራ በአንዳንድ ወገኖች በሌላ በኩል በኢህአዴግ መሪዎች ዘንድ ተቀባይነት የለውም። በተቃዋሚዎች ጎራ "እኛ በፓርላማ ሌላው ደግሞ በህዝባዊ ትግል" ብለው በጥንድ ስትራቴጂ እናምናለን የሚሉ ሃይሎች የድርድር ጉዳይ ሲመጣ ደግሞ "ወይ ከድርድር ወይ ከህዝባዊ ትግል" የሚል እንግዳ የሆነ ስትራቴጂ የያዙ ይመስላል። ኢህአዴግም መደራደር ከፈለጋችሁ ትግሉን አቁሙ፤ ትግል እንቀጥላለን ካላችሁ ደግሞ አልደራደርም የሚል አቋም እንዳለው ግልፅ ይመስለናል። ከመስከረም 23 እስከ 25 ተጠርቶ የነበረው የቤት መዋል አድማ የተሰረዘው ከዚህ "ወይ ከህዝባዊ ትግል ወይ ከድርድር" ከሚለው ግንዋል ስሌት በመነሳት እንደመሆኑ መጠን በቀጣዩ የትግል ስትራቴጂ ቦታ እንዳይኖረው መታገል ይኖርብናል። በኛ ግምት ከኢህአዴግ ጋር የሚደረገውን ድርድር እንደ ትግሉ አልፋ ኦሜጋ ሳይሆን በህዝባችን ዘርፈ ብዙ የነፃነት ተጋድሎ እንደ አንድ አካል ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል። ይህ ማለት ደግሞ ድርድር ህዝባዊ ትግሉን የሚያግዝ እንጂ በምንም አይነት ይህንን የሚተካ ስልት ሆኖ መቅረብ የለበትም ማለት ነው። በዚህ መልክ አንዱን ትተን ሌላው ላይ እናተኩር ከተባለ የህዝቡን ድል ለማስመለስ መደረግ ያለበትን ህዝባዊ ትግል በማያዋጣ የጥቂቶች መፍጨርጨር የመተካት ሂደት ስለሚሆን ህዝብን ግራ በማጋባትና በመከፋፈል በነፃነቱ ተጋድሎ፤ በህዝብ ትግል ኪሳራ የሚካሄድ በጣም አደገኛ ሂደት ነው እንላለን። ህብረታችንም ሆነ በአጠቃላይ የሃገራችን ዴሞክራቶች እዚህ አይነቱ 'ወጥመድ ውስጥ መግባት የለባቸውም።

አሁን ካለው በፓርላማ መግባት አለመግባትና በድርድሩ ጥያቄ በተነሱ ውዝግቦች የተነሳ ትንሽም ቢሆን ታጋዩ ህዝባችን ግራ የመጋባት ፍንጭ ከሚታይበት ሁኔታ ተላቆ ት-ግሉ አዲስ እምርታ ሊያገኝ የሚችለው በአንድ መንገድ ብቻ ነው። የሃገራችን ዴሞክራቶች በሚቀጥሉት ቀናትና ሳምንታት የህዝባችን ታሪካዊ የነፃነት ተጋድሎ መከተል ስላለበት አጠቃላይ ሂደት በአስቸኳይ አንድ አይነት ስምምነት መድረስና ለዚህም የትግሉ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያውቀው የጊዜ ሰሌዳ አውጥተው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል።

1ኛ. ከኢህአዴግ መሪዎች ጋር የተያዘው ድርድር እንዲቀጥል ብንፈልግም ይህ ሂደት ትግሉን በሚያቀዘቅዝና ብሎም ለአደገኛ ቅልበሳ በሚያመቻቸው መልክ መካሄድ ስለሌለበት ድርድሩንም ህዝባዊ ትግሉንም በአንድ ተጋጋዥ ሂደት ለማካሄድ መቁረጣችን ለህዝባችንም፤ ለኢህአዴግ መሪዎችም ለአለም አቀፍ ኮሙኒቲውም ግልፅ በሆነ መንገድ መገለፅ ይኖርበታል። የኢህአዴግ መሪዎች ወይ ከህዝብ ጋር ከመታገል ወይም ከኛ ጋር ከመደራደር ምረጡ የሚሉ ከሆነ በህዝብ ትግል ግፊት ትርጉም ወደሚኖረው ውይይት እስኪመጡ ድረስ ድርድሩን ማቋረጥ ያስፈልጋል።

2ኛ. የግንቦት 97 ምርጫ ውጤት ተብሎ በኢህአዴግ ምርጫ ቦርድ የቀረበውን የኢትዮጵያም ህዝብ ሆነ እኛ ዴሞክራት ልጆቹ እንደማንቀበለውደጋግመን አስታውቀናል። ይህ ማለት በህዝባችንም ሆነ በኛ አይን ከዚህ የሸፍጥ ሂደት የሚፈልቀው ፓርላሜንት ህገ ወጥ አካል ነው ብለን እናምናለን። በመሆኑም ይህ ፓርላማ መሰብሰብ በሚጀምርበት መስከረም 30 ቀን በመላ ኢትዮጵያ ለ48 ሰአት የሚፀና የቤት መዋል አድማ በማካሄድ ህዝባችን ያለውን ተቃውሞ ለመላው አለም እንዲያሰማ ጥሪ ማድረግ ያስፈልጋል።

3ኛ. ለዴሞክራታይዜሽንና ለብሄራዊ እርቅ የሚደረገው ተጋድሎ እየሰፋና ይበልጥ እየተቀነባበረ መሄድ ስላለበትና ይህ ታሪካዊ ተጋድሎ ከእንግዲህ አንዲት እርምጃም ቢሆን ወደፊት መራመድ የሚችለው ካሁኑ ይበልጥ ሰፍቶ ከፖለቲካ ድርጅቶች ውጭ ያሉትን የህብረተሰብ ሃይሎች በማካተት፤ ካሁኑ ይበልጥ ተቀነባብሮ እነዚህን ሁሉ

ሃይሎች በአገር አቀፍ ደረጃ አቀነባብሮ ሲቀጥል ብቻ ስለሆነ በያለበት በህዝቡ ውስጥ ተተክለው የሚዋደቁ ታጋዮችንና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተ ለመስከረም 20/21 ታስቦ የነበረውን አገር አቀፍ ጉባኤ ለጥቅምት 5..እና 6 መጥራት አስፈላጊ እርምጃ ነው።

4ኛ. የዚህን ጉባኤ ውሳኔዎች ለመደገፍና ለሚያቀርባቸው ጥሪዎች አወንታዊ መልስ ለመስጠት ህዝቡ ድምፁን ማሰማት ስለሚኖርበትና የኢህአዴግ መሪዎች በቁም ነገር ከህብረተሰቡ ጋር እንዲደራደሩ የህዝቡ ፍላጎት መሆኑን ለማረጋገጥ ለእሁድ ጥቅምት 13 ለመስከረም 22 ተጠርቶ የነበረው ህዝባዊ ሰልፍ አይነት መጥራት የሚሉት እርምጃዎች ካሁኑ ውሳኔ ተሰጥቶባቸው ባስቸኳይ ዝግጅቱ መጀመር ይኖርበታል።

ከመኢሶን
06/10/05